የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ-የካቲት ፳፭ ቀን ፪ሺ.ህ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 19
ADDIS ABABA-4th March, 2008

ደንብ ቁጥር ፩፻፵፮/፪ ሺ.ህ
ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የስራ መስኮች የወጣውን ደንብ ማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገጽ ፬ሺ.፳፬

CONTENTS

Regulation No. 146/2008
Council of Ministers Regulation to Amend the Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Regulation ............... Page 4024

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፮ /፪ሺ.ህ

## ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣውን ደንብ ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፮ እና ፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ «ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአ ገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፩፻፵፮ /፪ሺ.ህ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፬/፲፱፻፺፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩. የደንቡ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፫) እና (፭) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፫) እና (፭) ተተክተዋል፣

"፩. በማኑፋክቸሪንግ፣ በአግሮ ኢንዱስትሪ ወይም ቦርዱ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ በሚወሰኑ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት ኢንቨስትመንት መስኮች ወይም የግብርና ምርት ዓይነቶች ማምረት ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ባለሀብት ካመረተው ምርት ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ቢያንስ፣

## Council Of Ministers Regulation NO - 146 /2008
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE INVESTMENT INCENTIVES AND INVESTMENT AREAS RESERVED FOR DOMESTIC INVESTORS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Articles 6 and 9 of the Investment Proclamation No. 280/2002.

1. ***Short Title***

This Regulation may be cited as the "Investment Incentives and Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers (Amendment) Regulation No.146/2008".

2. ***Amendment***

The Council of Ministers Regulation No. 84/2003 is hereby amended as follows:

1/ Sub-articles (1), (3) and (5) of Article 4 of the Regulation are repealed and amended by the following new sub-articles (1),(3) and (5):

"1/ Where investor engaged in manufacturing, agro-industrial activities, or investment areas of information and communication technology development or the production of agricultural products to be determined by directives to be issued by the Board :

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ.፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

ሀ) ፶% (ሃምሣ በመቶ) የሚሆነውን የምርቱን ውጤት ወይም የሚሰጠውን አገልግሎት ወደ ውጭ የሚልክ ከሆነ፣ ወይም

ለ) ፸፭% (ሰባ አምስት በመቶ) የሚሆነውን የምርቱን ውጤት ወይም የሚሰጠውን አገልግሎት ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ወይም በአገልግሎት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ፣

ለ፭ ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል::"

"፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሱት ሥራዎች የተሠማራ ባለሀብት ካመረተው ምርት ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ከ፶% (ሃምሣ በመቶ) በታች የሚሆነውን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለሀገር ውስጥ ገበያ ብቻ የሚያቀርብ ከሆነ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል::"

"፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ቢኖርም፣ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለሀገር ውስጥ ገበያ ብቻ የሚያቀርብ ባለሀብት የመብቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ሊከለክል ይችላል::"

፪. የደንቡ አንቀጽ ፭ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፭ ተተክቷል፣

"፭ <u>ነባር ድርጅትን በማስፋፋት ወይም በማሻሻል ስለሚሰጥ የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተ ጠቀሱት የሥራ መስኮች የተሠማራና ከሚያመርተው ምርት ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ቢያንስ ፶% (ሃምሣ በመቶ) የሚሆነውን ወደ ውጭ የሚልክ ባለሃብት ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ከ፳፭% (ሃያ አም ስት በመቶ) በላይ በእሴት ካሳደገ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብት ያገኛል::"

፫. የደንቡ አንቀጽ ፱ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተተክቷል፣

a) exports 50% (fifty percent) of his products or services: or

b) supplies 75% (seventy five percent) of his product or services to an exporter as a production or service input:

shall be eligible for income tax exemption for 5 years."

"3/ An investor engaged in activities mentioned under sub-article (1) of this Article who exports less than 50% (fifty percent) of his products or services, or supplies his products or services only to the domestic market shall be eligible for income ax exemption for 2 years."

"5/ Notwithstanding the provision o sub-article (3) of this Article , directives issued by the Board may prohibit exemption from income tax with respect to an investor who supplies his products or services only to the domestic market."

2/ Article 5 of the Regulation is repealed and amended by the following new Article5:

"5/ ***<u>Income Tax Exemption for expansion or Upgrading of an Existing Enterprise</u>***

An investor engaged in activities mentioned under sub-article (1) of Article 4 of thise Regulation who exports at least 50% (fifty percent) of his products or services and increases, in value, his production or services by over 25% (twenty five percent) shall be eligible for income tax exemption for 2 years."

3/ Article 9 of the Regulation is repealed and amended by the following new Article 9:

“፱. <u>ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ስለሚፈቀድ ሁኔታ</u>

፩/ ማንኛውም ባለሀብት፣

ሀ) ለሠራተኞች የአደጋ ጊዜ አገልግሎት የሚውሉ አምቡላንሶችን፣
ለ) ለአስጎብኚነት ሥራ የሚውሉ አውቶቡሶችን፣ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፣

ሀ) ለአስጎብኚነት ሥራ የሚውሉ እስከ ፫ የሚደርሱ የመስክ ተሽከርካሪዎችን፣
ለ) ለሌሎች ኢንቨስትመንቶች እንደ ፕሮጀክቱ ዓይነትና ባህሪ የሚወስኑ ተሽከርካሪዎችን፣

ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል።”

፫ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

“9. ***Conditions for Importing Vehicles Duty Free***

1/ Any investor may import duty free:

a) ambulances used for emergency case of employees:

b) buses used for tour operation services.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, the Board may issue directives on conditions of importing duty free:

a) up to three 4-wheel drive vehicles for tour operation services:

b) Vehicles for any other investments depending on the type and nature of the project.”

3 *Effective Date*

This Regulation shall come into force up on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 4h day of March ,2008

MELES ZENAWI
PRIME MNISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA